# የታላቁ መሪ መለስ ዜናዊ አስተምህሮዎች

ፍቃዱ ሞላ 08-13-17



ነሐሴ 14 ቀን 2004 ዓ.ም ኢትዮጵያ ታላቅ መሪዋን በሞት ተነጠቀች። እኒህ ታላቅ ሰው በሞት ከተለዩን የዛሬ ሳምንትም አምስት ዓመት ይሞላቸዋል። የነሐሴ 15/2004 ዓ.ም ማለዳ የያኔው የኢትዮጵያ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ድርጅት፤ የአሁኑ የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን/ኢቢሲ/ ለኢትዮጵያውያንና ለመላው ዓለም አንድ ያልተጠበቀ የጠዋት መርዶ አረዳ - የታላቁ መሪ መለስ ዜናዊን ዜና ዕረፍት፡፡ በዓለም አሉ የተባሉ ታላላቅ መገናኛ ብዙሃን ዜናውን በመቀባበል በሰበር ዜና ሰፊ ሽፋን ሰጡት፤ በተለይም ታላላቆቹ ዓለም አቀፍ ሚዲያዎች ይህን ዜና ቀዳሚ ርዕሳቸው በማድረግ ስለ ታላቁ መሪ ብዙ ተናገሩ፤ ተከታታይ ፕሮግራምና ትንታኔም አቀረቡ።

ከታላቁ መሪ ዜና ዕረፍት ደቂቃ ጀምሮ እስከ ቀብር ሥነ-ስርዓት አፈፃፀም ድረስ የነበረውን ሁኔታና አጠቃላይ አገራዊ የሃዘን ድባብ ሁላችንም የምናስታውሰው ነው። መለስ ዓርዓያነት ህያው ይሆን ዘንድ ሁሉም በፀረ ድህነት ትግሉ እንደሚረባረብ ቃል ገብቷል። የተጀመሩ የልማትና የመልካም አስተዳደር ሥራዎችና የዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ ሂደቶችን ለማሳካት የሚደረገው ርብርብም ይበልጥ ተጠናክሮ እንዲቀጥል ሁሉም የበኩሉን እያከናወነ ነው።

ታላቁ መሪ መለስ ዜናዊ ስለራሱ መናገርም ሆነ መስማት አይወድም ነበር። ከአንደበቱ እንዳትወጣ ዕድል የተነፈጋት ቃል ብትኖር «እኔ» የምትለዋ ቃል ሳትሆን እንደማትቀር የሚወዱት የትግል ጓዶቹ ከተሰዋ በኋላ በሥርዓተ ቀብሩ ዕለት በሚወደው ሕዝብ ፊት መስክረውለታል።

ታላቁ መሪ መለስ ዜናዊ በዓለማችን አልፎ አልፎ ከሚከሰቱ የዓለም መሪዎች አንዱና ባለፉት 200 ዓመታት ከታዩ ባለ ምጡቅ አእምሮና ሰብእና ካላቸው መሪዎች(World Class Mind & World history personalities) የሚመደብ ነው። ለአገራችንና ለአፍሪካ እንዲሁም ለዓለም ጠቃሚ ሃሳቦችን በማመንጨትም ይታወቃል። በቡድን 7 እና ቡንድ 20 አባል አገራት በመሳተፍ ብቃቱን ያስመሰከረ የአፍሪካ ኩራት ነበር።

በታሪክ በህብረተሰብ ለውጥ ወሳኝ ሚና የሚኖራቸው ህዝብና ድርጅት ቢሆኑም ግለሰቦች ደግሞ የማይተካ ሚና አላቸው። እነዚህ ግለሰቦች በህዝብና በድርጅት እንቅስቃሴ ውስጥም ይፈጠራሉ። ታላቁ መሪ መለስ የፈጠረው የኢትዮጵያ ህዝቦች እንቅስቃሴና ድርጅቱ ነው። መለስ በኢትዮጵያ የነበረው ብሄራዊና ሃይማኖታዊ ጭቆና ትግል ውጤት ነው።

የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የተማሪዎች ንቅናቄ፣ የህወሓትና ኢህአዴግ ትግል ውጤትም ነው። ስለዚህ የመለስን ውርስ /ሌጋሲ/ ማወቅና ለተግባራዊነቱ መሥራት የአሁኑ የአመራር ትውልድና የመላው ህዝብ ሥራ መሆን አለበት። ምክንያቱም በመለስ የአመራር ዘመን የተጀመሩና የኢትዮጵያ ህዳሴን ዕውን የሚያደርጉ ሥራዎች አሁንም አሉና። እነዚህን ሥራዎች በማሳካት የኢትዮጵያን ህዳሴ ዕውን በማድረግ የበለፀገች አገር ለመፍጠር ስለሚቻል ነው።

ታላቁ መሪ ሲታወስ አንደኛ ጉዳይ በህዝቦች መካከል የነበረው፣ ያለውንና ያልተስተካከለውን፣ እንዲሁም ፍትሃዊ ያልሆነውን ግንኙነት ለማስተካካል ጠንክሮ ሰርቷል። ህዝቦች በመደጋጋፍ ድህነትና ኋላ ቀርነትን ለማስወገድ እንዲሠሩ፣ ቀና ግንኙነትና ዝምድና እንዲኖራቸው ጥረት አድርጓል። ሁሌም ነገሮችን የሚመለከታቸው ከጭቁኖች ወገን ሆኖ ነው። ለአርሶ አደር፣ ለወጣቶች፣ ለጭቁን ህዝብ ኑሮ መለወጥ ነው ሲተጋ የኖረው።

ሁለተኛው ጉዳይ መለስ በሰዎች መካከል ብቻ ሳይሆን በሰዎችና በተፈጥሮ መካከልም ሚዛናዊ ግንኙነት እንዲኖር ለማድረግም ሰርቷል። በአየር ንብረት ለውጥ የሚከሰተውን አደጋ ለመከላከልና ተፈጥሮ ለሰው ልጆች ምቹ ትሆን ዘንድ በአካባቢ ጥበቃ ሥራ ላይ ትኩረት ተደርጎ እንዲሠራም ሌት ተቅን ለፍቷል። ይህን ሲሠራም ታሳቢ የሚያደርገው ጭቁን ህዝቦችን ተጠቃሚ ከማድረግ አይታ ነው። ጭቁን ህዝቦች ሲባል የኢትዮጵያ ጭቁን ህዝቦች ብቻ ሳይሆኑ በመላው ዓለም የሚገኙትን ታሳቢ በማድረግ ነው። ይህ ደግሞ ከህዝባዊነቱ የሚመነጭ ነው፤ ህዝባዊነት ደንበር የለውምና። ስለሆነም ሌጋሲውንና አስተምህሮውን ለትውልድ ማሳወቅ ተገቢ ነው።

የመለስ ሌጋሲና አስተምህሮን የማስቀጠል ፋይዳ ህዝቦች ያገኙትን የተስፋ ጭላንጭል ቀጣይነት እንዲኖረው ማድረግ ነው። የመለስ ሌጋሲና አስተምህሮ ባለቤቱ ደግሞ ይህንን ተቀብሎ ዳር ላይ የሚያደርስ እና ህዝቦች ከድህነት እንዲወጡ በተግባር መሥራት የቻለ ነው። ይህ ማለት በአገር ውስጥ ብቻ ሳይሆን በዓለምም ጭምር ነው። ምክንያቱም የመለስ አስተምህሮ እና እሴቶች የዓለም ሀብት(Global Asset)ናቸውና።

**የመለስ አስተምህሮዎች፡-**

**የላቀ ህዝባዊ ውግንና**

በትጥቅ ትግሉ ወቅት ኢህአዴግ ደርግን የጣለው ህዝቦችን በማንቃትና በማስታጠቅ ነው። ከደርግ ውድቀት በኋላ ልማቱን ማፋጠን የቻለውም ከህዝብ ጋር ሆኖ ነው። መለስና ኢህአዴግ ህዝብ ሲሉ ጭቁን ህዝቦችን ማለታቸው ነው። ይኸውም አርሶ አደር፣ ላብ አደር፣ የከተማ ጭቁን ህዝብ፣ ሴቶች፣ ወጣቶች ወዘተ ...ማለታቸው ነው። የእነዚህን ህዝቦች ችግር መፍታት ዋናው ተግባራቸው ነው። የሚሠሩትም የታገሉትም የእነዚህን ህዝቦች ችግር ለመፍታት ነው።

መለስ ከትጥቅ ትግል ጊዜ ጀምሮ ጥናት ሲያደርግ፣ ሲመራመርና ሲገመግም ዋና ዓላማው እነዚህን ጭቁን ህዝቦች ተጠቃሚ በማድረግ

ነው። ለመለስ ህዝብን ማገልገል ማለት የህዝብን ችግር መፍታት ነው። ይህ ማለት ደግሞ ድህነትና ኋላቀርነትን ማስወገድ ነው። ድህነትን ዋና ጠላት ያላደረገ መሪ መሪ አይደለም ይልም ነበር። ምክንያቱም ጭቁን ህዝቦች ከድህነት መውጣት ካልቻሉ መሪ መሆን ዋጋ የለውም ማለት ነው።

መለስ ለህዝብ የላቀ ውግንና አለው ሲባል ብሄርና ደም አያይም። ሁሉም ህዝብ ህዝብ ነው። በየትኛውም አገር ይኑር ህዝብ ህዝብ ነው። ስለ ሰላም፣ ልማትና ዴሞክራሲ ሲያስብም ህዝቦችን ታሳቢ በማድረግ ነው። የመለስ ህዝባዊነት ለኢትዮጵያ ህዝብ ብቻ አይደለም። ለዓለም ጭቁን ህዝቦችም ልሳን ነበር። የልማታዊ ዴሞክራሲያዊ አስተሳሰብ ዋና ማሰሪያው፣ መነሻና መድረሻው ከመደባዊ ትንተናውና ከህዝብ ተጠቃሚነት አንፃር በማየት ነው።

**አይበገሬና የፅናት ተምሳሌት**

ኢህአዴግና አባል ድርጅቶቹ ፈተናዎች ያጋጥሟቸው ነበር። እነዚህ ፈተናዎች በዓላማ ፅናት እየታገሏቸው በድል ተረማምደው እዚህ ደርሰዋል። መለስም በድርጅቱ ውስጥ አጋጥመው በነበሩ ፈተናዎች በጽናት በማለፍ በኩል የአይበገሬና የፅናት ተምሳሌት ነው። የመለስ አይበገሬነትና የፅናት ተምሳሌትነት በአራት ዋና ዋና ጉዳዮችን በማንሳት ማሳየት ይቻላል።

አንደኛው በ1977 ዓ.ም በህወሓት ውስጥ አጋጥሞ በነበረው የትግል መቀዛቀዝ ወቅት ያሳየው ፅናትና አይበገሬነት ነው። ወቅቱ የድርጅቱ አላማ ዳር ለማድረስ የሚያዳግትበት ሁኔታ የተፈጠረበት፣ ወደ ማቆም አዝማሚያ የታየበት፣ የርእዮት ዓለም መዳከምና የአብዮታዊነት መቀዛቀዝ የታየበት አደገኛ ሁኔታ ነበር። መለስ ድርጅቱን ከዚህ የመቆም አዝማሚያ ለማዳን በጥናትና በምርምር የተደገፉ ሃሳቦችን ይዞ በጉባኤ በሃሳብ አሸንፎ ድርጅቱን መታደግ የቻለ መሪ ነው። ይህን ሲያደርግ ግን በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ሆኖ ቢሆንም በፅናት ፊት ለፊት የሃሳብ ትግል ማካሄድ ችሏል።

ሐምሌ ወር 1977 ዓ.ም ለሁለት ሳምንታት በተካሄደው ጉባኤ የተፈጠሩት የሃሳብ ልዩነቶች ወደ ግጭት ሳይሄዱ በሃሳብ ትግል በውይይት እንዲፈቱ ተደርጓል። ይህ ጉባኤ ሲካሄድ የመለስ ሚና ከፍተኛ ነበር። መለስ

ከ1972ዓ.ም ጀምሮ ሳይንሳዊ ምርምር በማካሄድ ወታደራዊ ታክቲክና ስትራቴጂ፣ የህዝብ አደረጃጀት፣ የውጭ ግንኙነት፣ የደፈጣ ውጊያ አዋጭ አለመሆኑን... በተመለከቱ ጉዳዮች ላይ የነበሩትን ልዩነቶች በሃሳብ ትግል በፅናት ታግሎ ማሸነፍ የቻለ በሳል መሪ ነው። በሃሳብ የተከራከራቸው የድርጀቱ ቁንጮ መሪዎች የነበሩትን ነው። ይህ ደግሞ ለህዝብ ጥቅም ሲባል በአይበገሬነትና በፅናት የመታገል ተምሳሌት ያደርገዋል። አዲሱ ትውልድ በዓላማ እስከ መጨረሻው መታገልን መማር ይኖርበታል። ለአድርባይነት ቦታ መስጠትም የለበትም።

ሁለተኛው በኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት ወቅት የያዘው አቋም ነው። ጦርነቱ በሰላም ይፈታ፣ ከድህነት ለመውጣት የሚደረግ ጥረትን ያዘናጋል፣ ቅድሚያ ለሰላም ይሰጥ ይህ ከተሚጠጠ ግን በአጭር ዝግጅት መደምሰስ የሚችል አቅም በመገንባት ሉኣላዊነትን ማስከበር ይቻላል የሚለው አቋሙ በአብዛኛው የሥራ አስፈፃሚ ተቀባይነት ባያገኝም እስከመጨረሻው ታግሏል። የኤርትራ ህዝብን እንደ ጠላት

የሚያይ አስተሳሰብንም ኮንኗል። ሻዕብያንና የኤርትራ ህዝብን ደምሮ አንድ ላይ በጠላትነት የሚፈርጅ አተያይ ስህተት መሆኑን በፅናት ታግሏል።

ጦርነቱ ይካሄድ የሚለው ሃሳብ አሸናፊ በሆነበት ደግሞ ጦርነቱን በአጭር ጊዜና በአነስተኛ ኪሣራ ለማጠናቀቅ የሚያስችሉ መጽሐፎችን ፅፎ በተግባር በማዋል ውጤታማ ሥራ ሠርቷል። ጦርነቱ ከተጠናቀቀ በኋላ ደግሞ ዓለም የተቀበለው ባለ አምስት ነጥብ የሰላም ሃሳብ በ1994 ዓ.ም በመቅረጽ በፓርላማ ማፀድቅ ችሏል።

ሦስተኛው የ1993 ዓ.ም ተሃድሶ ነው። በዚህ ወቅት ከአንጃው ይደርስ የነበረውን ተፅእኖ በመቋቋም በሃሳብ ትግል ልዩነቶችን ለመፍታት በፅናት ታግሏል። በዚህ የሃሳብ ትግል ወደ 13 የሚጠጉ መጽሐፎችን ፅፎ ነው በፅናት የተከራከረው። ኋላም አገሪቱ የምትመራባቸው ፖሊሲዎችና ስትራቴጅዎችን በማውጣት ፈጣንና ተከታታይ እድገት እንዲመዘገብ በፅናት መርቷል።

አራተኛው ከውጭ ኃይሎች የሚነሱ ተፅእኖዎችን በፅናት መታገል ነው። የኒዮ ሊበራል ኃይሎች ብድርና እርዳታ ለመስጠት ፖሊሲያቸውን ለመጫን የሚያደርጉትን ጫና መቀነስ ችሏል። የፖሊሲ አማራጭን ለብድርና እርዳታ አናከራይም ብሎ ሞግቷል። አቋሙን በሳይንሳዊ መንገድ ተንትኖ የማስረዳት አቅም ነበረው። ለአገር ውስጥ እና ለውጭ ባለሀብቶች የተፈቀደውን በግልፅ ማስቀመጥ ችሏል። መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እንዴት መደራጀት  እንዳለባቸው በተለይ በፖለቲካ ጉዳይ መሳተፍ የማይችሉ መሆኑን በፅናት አቋሙን አሳይቷል። ጠንካራና ትልቅ መንግሥት ለልማት አስፈላጊ መሆኑን በንድፈ ሃሳብ ብቻ ሳይሆን በተግባር ማሳየት ችሏል። መንግሥት በገበያ ጉድለት ጣልቃ በመግባት ክፍተቱን መሸፈን መቻል አለበት ብሎ አቋም ይዟል። በዚህ ጉዳይ የምዕራባዊያንን ጫና ላለመቀበል በፅናት ታግሏል።

በአጠቃላይ መለስ ለህዝቦች ለውጥና እድገት፣ ከድህነት እንዲወጡ የሚያስችለውን ልማታዊና ዴሞክራሲያዊ መስመርን ከማንኛውም ተፅእኖ ነፃ ሆኖ ተግባራዊ ይሆን ዘንድ በአይበገሬነትና በፅናት የታገለ ታላቅ መሪ ነው።

**ሳይንሳዊና ተራማጅ አስተሳሰብና ተግባር የሚያራምድና የሚቀበል**

መለስ  ሁሌም ተራማጅና ሳይንሳዊ አስተሳሰብ ይዞ የሚራመድ ነው። ሁሌም ከወቅቱ ሁኔታ ጋር ተንትኖ ነገሮችን ያያል። በዚህም ተራማጅና ሳይንሳዊ አስተሳሰቦችን ይዞ ይሄዳል። ሲያነብ፣ ሲመራመር ሁሌም የህብረተሰብ ህግጋትን መሰረት በማድረግ ከተራማጅ ኃይሎች ጎን በመቆም፣ ተራማጅ ኃይሎችን ማብቃትና ማሰማራት ላይ ትኩረት አድርጎ ይሠራል።

ከደርግ ወድቀት በፊት በነበረው ሁኔታ የኢህአዴግ አባል ድርጀቶች ለመድረኩና ለንኡስ መድረኩ እንዴት መሥራት እንዳለባቸውና ፀረ ደርግ ትግሉን በአጭር ጊዜ ለማጠናቀቅ የሚያስችሉ ሃሳቦችን በማመንጨት ተግባራዊ እንዲሆኑ ሠርቷል። የህዝብን ማዕበል ተጠቅሞ ደርግን በአጭር ጊዜ በማስወገድ በከተማ ሊያጋጥም የሚችል ፈተና ምን ሊሆን እንደሚችልና መፈትሄውን የያዘ ፅሁፍ በ1982ዓ.ም ፅፏል። ይኸውም ጠንካራ ደጀን መመስረት፣ መደበኛ ሠራዊት የሰላ ጫፍ መሆኑን፣ የፓርቲ ርእዮት ዓለምን ማጥራትና የማስረፅ /ኢንዶክትሪኔሽን/ በግልፅ በማስቀመጥ ተግብሯል።

ከደርግ ውድቀት በኋላ ደግሞ በተለወጠ ዓለም ውስጥ ህዝቡ የማይፈልገው ስርዓት መገንባት ፀረ ዴሞክራሲ በመሆኑ፣ ዓለም ከቀዝቃዛው ጦርነት በኋላ በአንድ የበላይነት/አሜሪካ/ ጥላ ስር ላይ መውደቋን መለስ የገመገመው በጥር ወር 1982 ዓ.ም ነው። ስለሆነም ዴሞክራሲያዊ አብዮቱን በድል የማስቀጠል ጉዳይ ዋነኛ ጥያቄ ነበር። ድህነት መወገድ ነበረበት። ስለሆነም የአብዮታዊ ዴሞክራሲ አመራር የዳበረ ካፒታሊዝም ለመገንባት እና ማህበራዊ መሰረቱን ከድህነት የማውጣት የተቀደሰ አላማ በመሆኑ በልማታዊ ዴሞክራሲያዊ መስመር ካፒታሊዝምን መገንባት የሚቻል መሆኑን አስረድቶ ተግባራዊ አደረገ።

መለስ የህዳሴ ጉዟችንና የአመራር ግንባታ በሚል በፃፈው መጽሐፍም የዴሞክራሲ እንቅፋቶች ያላቸውን የብሄር ብሄረሰቦች መብት አጠቃቀም፣ ኪራይ ሰብሳሳቢው ኃይል ስላለ ስርዓቱን የሚፈታተን መሆኑ፣ ፀረ ዴሞክራሲያዊነት፣ አድርባይነት፣ ትምክህትና ጠባብነት መሆናቸው፣ ሁሉም ግን የጥገኞች መጠቀሚያ ስለሆኑ ሁሉም የየራሱን ጥገኛ ኃይል ሊታገል የሚገባው መሆኑን አስቀምጧል። በዚህም ልማታዊነት የበላይነት መያዝ የሚችል መሆኑን አመላክቷል።

አብዮታዊ ዴሞክራት ኃይሉ ባህሪውን ጠብቆ ከሄደ የልማታዊ ፖለቲካል ኢኮኖሚ ተልእኮ ማሳካት የሚችል መሆኑን፣ ሥልጣንን ለግል ጥቅም የመጠቀም ዝንባሌ ካለ ግን ህዝቡን ብቻ ሳይሆን አለአግባብ የተጠቀመውንም የሚያጠፋ መሆኑን አስፍሯል። ለመለስ ሥልጣን ማለት ለህዝቦች ማገልገል ማለት ነው። ህዝቦችን ከድህነት ለማውጣት መጠቀም ነው።

**በመርህና በሕግ የበላይነት የሚያምን**

*መለስ የሕግ የበላይነት ሲኖር ዴሞክራሲ ይኖራል፣ ዴሞክራሲ ሲኖር ደግሞ ድህነትን ማስወገድ ይቻላል ይላል።* መርህ የሌለው ሰው ችግር ፈጣሪ ነው። ማንም ሰው የመሰለውን ሃሳብ መያዝ ትክክል ነው ይላል፣ ነገር ግን ተቀባይነት ሳያገኝ ሲቀር ደግሞ የብዙሃኑን የመቀበል መርህን ማክበር አለበት ሲልም አስተምሯል ።

መለስ ዴሞክራሲያዊ እሴቶችን የሕይወት መመሪያው ያደረገ፣ በሕግ የበላይነት የሚያምን፣ ራሱንና የመንግሥት ባለሥልጣናትንና ድርጅቱን ከሕግ በታች እንጂ ከሕግ በላይ አድርጐ የማይመለከት በሳል መሪ ነው፡፡ የድርጅት እንቅስቃሴ በድርጅታዊ ሕገ ደንብ እንዲመራ የመንግሥትንና የድርጅትን ሚና ግልጽ በማድረግ ጣልቃ ገብነትን ያስወገደ፣ የመንግሥትና የሕዝብ አስተዳደርም በሕግ ማዕቀፍ ውስጥ እንዲከናወን አበክሮ የታገለና የሕግ የበላይነት የሰፈነባት አገር ለመፍጠር ቀን ከሌት የደከመ መሪ ነው፡፡ በድርጅት ውስጥ የሚያጋጥሙ ልዩነቶች በዴሞክራሲያዊ ውይይት እና በሃሣብ ትግል መፈታት አለባቸው የሚል ፅኑ ዕምነት ስለነበረው ልዩነቶች አያስደነግጡትም፡፡ ያመነበትን ሃሣብ በግልጽና በሕጋዊ መድረክ ላይ አቅርቦ ይከራከራል፡፡ የሚያምንበት ሃሣብ በብዙኃኑ ተቀባይነት ካላገኘ የብዙኃኑን ሃሣብ ተግባራዊ ለማድረግ ጥረት ያደርጋል፡፡ እዚህ ላይ እንደምሳሌ ሊጠቀስ የሚቻለው ከኤርትራ ጋር በተካሄደው ጦርነት ወቅት የነበረው አቋም ነው፡፡ መለስ የኤርትራን ወረራ ለመቀልበስ የኃይል እርምጃ የመጨረሻው መፍትሔ ነው፤ ተቻኩለን ወደ ጦርነት መግባት ለአገራችን አይጠቅምም የሚል አቋም ነበረው፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ በተደረገው ክርክር የብዙኃኑን የኢህአዴግ አመራር ድጋፍ ባለማግኘቱ ራሱን ለብዙኃኑ ውሳኔ በማስገዛት በሙሉ ልብ ወደ ሥራ ገብቷል፡፡

በተሃድሶ ዋዜማ በድርጅት ውስጥ የተከሰተውን ችግር ለመፍታት የተከተለው አቅጣጫ መለስ በአስቸጋሪ ወቅትም ቢሆን

ለዴሞክራሲያዊ መርሆዎች ያለውን ታማኝነት ያረጋገጠ ነበር፡፡ የችግሮቹን መሠረታዊ ምንጭ በማጥናት እና በመተንተን በጉዳዩ ላይ ያለመታከት በመወያየትና በመከራከር እስከ መጨረሻው ተንቀሳቅሷል፡፡

መለስ ለዓለም አቀፍ ሕግና ሥርዓትም ራሱን ያስገዛ መሪ ነው፡፡ የኤርትራ መንግሥት በአገራችን ላይ ወረራ በፈፀመበት ወቅት መለስ ከስሜትና ጀብደኝነት ነፃ በሆነ አስተሳሰብ የችግሩ ቀዳሚ መፍትሔ ዓለም አቀፍ ሕግ እንዲሆን አቅጣጫ አስቀምጧል፡፡ በመሆኑም የኤርትራ ጦር ወደ ነበረበት እንዲመለስና ችግሩ ዓለም አቀፍ የዳኝነት መድረክ እንዲፈታ ትክክለኛ አቋም ወስዷል፡፡ በዓለም አቀፍ የዳኝነት መድረክ የተወሰኑ ውሳኔዎች አንዳንዶቹ ችግር ያለባቸው ቢሆኑም ውሳኔውን በመቀበል ተግባራዊነቱ ዘላቂ ሰላምና ጉርብትናን በሚፈጥር መልኩ በድርድር እና በሰጥቶ መቀበል መርህ ማዕቀፍ እንዲታይ አቋም በመውሰድ ለሕግ የበላይነት ብቻ ሳይሆን ለዘላቂ ሰላም የአመራር ብቃቱን አሳይቷል፡፡

**ትልቅ ራዕይ ያለው**

የኢህአዴግንና የአገራችንን ራዕይ በመቅረፅ ረገድ መለስ ጉልህ ድርሻ አለው። የአንድ የትግል ምዕራፍ ሳይጠናቀቅ ለሚቀጥለው ምዕራፍ ይዘጋጃል። ደርግ ከመደምሰሱ በፊት ከደርግ ውድቀት በኋላ የበለፀገ አገር እንዴትና መቼ እንደሚገነባ ተንትኖ ማስቀመጥ  የቻለ ባለ ራዕይ መሪ ነው። ስለ አየር ንበረት ተፅእኖ፣ ስለ ዓለም ፖለቲካ... ቀድሞ ይተነትናል። ድንበር ተሻጋሪ ተንታኝ ነው። የዓረቡን ዓለም የፀደይ አብዮትና የአሜሪካ የፋይናንስ ቀውስን ቀድሞ መተነትን የቻለ በሳል መሪ ነው።

**በትልቁ የሚያስብ በትልቁ የሚተገብር**

መለስ የህብረተሰብ ለውጥ በአጭር ጊዜ መምጣት አለበት የሚል፣ ከድህነት ቶሎ መውጣት አለበት ብሎ የሚያምን ስለሆነ በትንሽ ድል አይረካም። በትንሽ ድል የሚረካ አመራር ትክክል አይደለም ብሎ ያምናል።

መለስ የህዳሴው ጉዞ ከተጀመረ በኋላም በተለይም በመጀመሪያዎቹ ሁለትና ሦስት ዓመታት በተገኙት ለውጦች አልረካም፡፡ የልማቱ ፍጥነትና ስፋት ሁሌም እንዳሳሰበው ነበር፡፡ «በገጠር የተገኙትን መልካም ውጤቶች በላቀ ፍጥነትና ጥራት ካላስፋፋን፤ ወደ ኋላ የቀሩትን ከተሞቻችንን ተአምራዊ ሥራ ሠርተንና ገለባብጠን ካላሻሻልናቸው፤ ባስቀመጥናቸው አዳዲስ መስመሮችና አሠራሮች ድርጅታችንን ሙሉ በሙሉ ካላደስነው፣ የወጣቶችንና የሴቶችን ችግሮች ቀልጥፈን ካልፈታን፣ ወጣቶችን ከድርጅታችን ጎን በሚሊዮኖች አሰልፈን መልካም ተሞክሮዎቻችንን አጋርተን የትግሉ ዋነኛ ባለቤቶች ካላደረግናቸው አስቸጋሪ ሁኔታ ይፈጠራል፤ እንፍጠን! »ነበር የዘወትር ሃሳቡና የሥራውም መመሪያ፡፡

ታላቁ መሪ በአንድ ወቅት የአገራችንን የድህነት ሁኔታና የርምጃችንን ፍጥነት እጅግ በሚያስገርም የንጽጽር አገላለጽ እንደሚከተለው አስቀምጦት ነበር፡፡ «የእኛ ጉዞና ከተራራ ጫፍ የሚወርድ ናዳ  ይመሳሰላሉ፡፡ ከላይ ከሚወርድ ናዳ ለማምለጥ የሚሮጥ ሰው ከናዳው የላቀ ፍጥነት ከሌለው ናዳው በጀመረበት የመጀመሪያም ሆነ በመጨረሻው ሰዓት ላይ ቢሞት ያው ሞቷልና በመጀመሪያውም ሆነ በመጨረሻው ሰዓት መሞቱ ትርጉም የለውም፤ ስለዚህም አገራችንን፣ መንግሥታችንንና ድርጅታችንን ሊበታትን ከሚችለው ናዳ እጅግ

በላቀ ሁኔታ መፍጠን ይገባናል» ስለዚህም የመለስ የርብርብ ማዕከል የሥራ ጥራት፣ ፍጥነትና ስፋት ነበሩ፡፡

ለመለስ ከድህነት በላይ አዋራጅ ነገር የለም፤ በድህነት የተቆራመዱና ጠኔ እየገረፋቸው የሚኖሩ፣ የሚለብሱት አጥተው በእርዛት የሚቸገሩና በመጠለያ እጦት ምክንያት ባረጁ ጐጆዎች ተፋፍገው የሚያድሩ ዜጐች አገር ይዘን እንቅልፍ ተኝተን ልናድር አይገባንም፡፡ ስለዚህም ጠላታችን የሆነውን ድህነትን በማጥፋት ዜጐቻችንን ሰብአዊ ክብር ማላበስ፤ አገራችንንም ከተስፈኞች ጐራ ማውጣት አለብን የሚል ፅኑ አቋም ነበረው፡፡ ከዚህ አኳያ የአገራችን ዕድገት ጐልቶ እንዲታይ ያደረጉት የከተማና የገጠር ልማት ፖሊሲዎች የአፈፃፀም ሥልቶች በምሳሌነት ይጠቀሳሉ፡፡

መለስ በውስን ግብና በመጠነኛ ውጤት የማይረካ፤ ታላላቁን የሚመኝ የሚደፍርና የሚያደፋፍር መሆኑ በግልጽ የታየበት ሌላው ታላቅ አብነት የታላቁ የህዳሴ ግድብ እቅድ ነው፡፡ ሌሎች ሊፈፅሙት ይቅርና ሊያስቡትም የማይደፍሩትን በአባይ ወንዛችን ላይ ከአፍሪካ በትልቅነቱ ቀዳሚ የሆነውን ታላቁን የህዳሴ ግድብ የመገንባት እቅድ አረቀቀ፡፡ ለግድቡ ሥራ ከፍተኛ ገንዘብ እንደሚጠይቅና ይህንንም ከውጭ ብድርና ርዳታ ማሟላት እንደማይቻል ቢገነዘብም የኢትዮጵያን ሕዝብ የቆየ ቁጭትና የልማት ቀናኢነት ከፍተኛ ሀብት እንደሆነ አርቆ በማስተዋል አይቻልም ባይነት ላይ የክተት አዋጅ እንዲታወጅ አድርጓል፡፡ ግድቡም ዛሬ ስድስተኛ ዓመቱን ያስቆጠረ ሲሆን፤ ግንባታውም 60 በመቶም ደርሷል።

**በሣይንስና በዕውቀት ላይ ተመሥርቶ የመመልከት ብቃት**

መለስ ነገሮችን ሲያይ ከስሜት ውጭ ሆኖ በሣይንስና በዕውቀት ነው። *«ህዝብ ስትመራ ህዝበኝነትን አስወግድ፣ ዕውነቱን ተናገር፣ ሥራ ስትገመግም አወንታ ሲጎላ ትንሿን አሉታ መሰረት አድርገህ ገምግም፣ አሉታ ሲበዛ ደግሞ አወንታውን አጉልተህ ገምግም። ለሁሉም ግን መነሻና መፍትሄ አስቀምጥ»* ይላል።

መለስ ገና ከጎልማሳነቱ ጀምሮ ዕውቀትን ለማካበት በእጅጉ ይጥር ነበር፡፡ ድህነትን መግደል የሚቻለው በዕውቀት ጥይት ነው የሚል መርህን የሚከተለው መለስ ቀን ከሌት በማንበብና ከሰዎች ጋር በመወያየት ዕውቀቱን የማዳበር ልዩ ተሰጥኦ ነበረው፡፡ መለስ ዕውቀቱን የሚያዳብረው የያዘውን ዓላማ ከግብ ለማድረስ የሚያስችለውን አቅም ለመፍጠር ነው፡፡ የትግሉን መስመሮች ለመንደፍ የተለያዩ አገሮችን ልምድ አጥንቷል፣ የተለያዩ የኢኮኖሚ ዘርፎችን መርምሯል፣ የወታደራዊ ሣይንስ መድበሎችን አገላብጧል፡፡ ከዚህ የካበተ የዕውቀት ባህል ለትግሉና ለአገሩ የሚጠቅሙ ልምዶችን የመቀመር ከአገራችን ሁኔታ ጋር አስተሳስሮ የመተንተንና የመጠቀም አቅም አዳብሯል፡፡

መለስ ማንኛውም አስተሳሰብ መመዘን ያለበት ለሰፊው ሕዝብ ከሚያስገኘው ፋይዳ አኳያ ነው የሚል ፅኑ ዕምነት አለው፡፡ ከግራ ዘመም የፖለቲካ ታሪክ የትግል እርምጃውን የጀመረው መለስ ያ አቅጣጫ ከሕዝቡ ጥቅም አኳያ ሚዛን የማይደፋ ሆኖ ሲያገኘው እርሱን አሽቀንጥሮ ለሕዝቡ የሚጠቅመውን ለማገናኘት ዓይኑን ያላሸ፣ ከሁኔታዎች ጋር የሚራመድ፣ ነገር ግን ዋነኛ ዓላማውንና መርሁን የማይለቅ መሪ ነው፡፡ በርካታ የውጭ መሪዎች መለስ በመሰረታዊ አገራዊ ጥቅም ላይ የማይደራደር መሆኑን በአድናቆት ይገልፃሉ፡፡ ይህ ሰፊ የዕውቀት አድማስ አዲስና ስርነቀል የፖለቲካ ኢኮኖሚ ለውጥ የሚያመጡ ፖሊሲዎች ለማፍለቅ፣ እጅግ የገዘፈ ራዕይና

ለማመን የሚያስቸግሩ የተለጠጡ ግቦችን ያለሙ ዕቅዶችን ለማውጣት ረድቶታል፡፡ የመለስ የዕውቀት ልህቀት አዳዲስ አስተሳሰቦችንና በምክንያታዊ ዘይቤዎች የተቃኙ መሰረታዊ መርሆዎችን መንደርደሪያ ያደረጉ የችግር አፈታት ጥበቦችን ያስተሳሰሩ በመሆናቸው ሁልጊዜም ውጤታማ ነበሩ፡፡

**ለዴሞክራሲ የቆመ መሪ**

መለስ ገና ከጠዋቱ አገራችን ኢትዮጵያ የብሔሮችና የሃይማኖቶች ብዝሀነት ያቀፈች እንደመሆኗ ልዩነታችንን አክብረን የተዘነጉ፣ የተናቁ ማንነታቸውና ዕኩልነታቸው ዕውቅና አግኝቶ የአገሪቷ ዴሞክራሲያዊ አንድነት ነፃና ሕያው አካል እንዲሆኑ በሰፊው ጥሯል፡፡ የአገሪቱ ዓብይ ኃይል አርሶና አርብቶ አደሩ ነውና የኢትዮጵያ የዴሞክራሲም ሆነ የልማት መሠረት ገጠሬው እንደሆነ አሳይቷል፡፡ ብዝሃነትን ማክበር የአገሪቱ ህልውና መሠረት መሆኑን አፅንኦት ሰጥቶ አስተምሯል፡፡ በገዛ አገራቸው ተዘንግተው የኖሩ፣ የተናቁና ማንነታቸውና ዕኩልነታቸው የተገፉ ወገኖች ዕኩልነታቸው ታውቆ በአገሪቱ ወሳኝ ተግባራት ተሳታፊና የውጤቱም ዕኩል ተጠቃሚ እንዲሆኑ በዚህም የአገሪቱ ዴሞክራሲያዊ አንድነት ነፃና ህያው አካል እንዲሆኑ በሰፊው ተንቀሳቅሷል፡፡ ይህ እሳቤ ለትግሉ እርምጃ መስፋፋት፣ ለሽግግሩ ስምሪት፣ ሕገ መንግሥቱ የምልዓተ ሕዝብ ተቀባይነት አግኝቶ ዕውን እንዲሆን ለማድረግ እንዲሁም የአገሪቱ ፖሊሲዎች የአገሪቱን ነባራዊ ገጽታ የሚያንፀባርቁ እንዲሆኑ ለማስቻል ዋነኛ ማጠንጠኛ ሆኖ እንዲያገለግል ለማድረግ መለስ በእጅጉ ተንቀሳቅሷል፡፡

የአገራችን ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሕገ መንግሥት የመላ የአገራችን ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የጋራ ቃልኪዳን ሆኖ እንዲፀድቅ ያለፉ ቁርሾዎችንና ጥርጣሬዎችን በሚያስወግድ መልኩ ጐልብቶ እንዲወጣ መለስ ያደረገው ተጋድሎ ለአገራችን ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ያለውን ፅኑ ፍቅርና አክብሮት ያረጋገጠ ነው፡፡ በዕኩልነት፣ በመከባበርና በመፈቃቀድ ላይ የተመሠረተ አንድነት ማስፈን ካልቻልን አንድ የጋራ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ማኅበረሰብ መፍጠር የሚባል ነገር ህልም እንደሆነ መለስ በተደጋጋሚ ያስተምር ነበር፡፡

መለስ ሰውና ሃሳብ ለይተህ ግምገማ አካሂድ፣ የጦፈ ክርክር ከተካሄደ በኋላ ከአንተ ጋር የተከራከሩትን በዴሞክራሲያዊ መንገድ ቅረባቸው ይላል። በድርጅትና በህዝብ ከሚካሄዱ እንቅስቃሴዎች መራቅ የለብህም የዴሞክራሲ ትምህርት ቤቶች ናቸውና።

መለስ ልማትና ዴሞክራሲ የማይነጣጠሉ መሆናቸውን ለመጀመሪያ ጊዜ የቀመረ ነው። ዴሞክራሲ ከሰው ጋር ተያይዞ መታየት አለበት። ዋናው የሰዎች ህይወት መቀየር ነው። መጠለያ፣ ምግብ...ማግኘት አለባቸው። ይህን ማድረግ ካልቻለ ዴሞክራሲ ዋጋ የለውም ሲል አስተምሯል። ዴሞክራሲ ከመጀመሪያው በጥልቀትና በስፋት መጀመር አለበት፣ ጥያቄዎችም በሰለጠነና በዴሞክራሲያዊ መንገድ መፈታት አለባቸው ብሎም አስተምሯል።

**ተማሪም አስተማሪም ተመራማሪም**

መለስ ከአርሶ አደር፣ ከአርብቶ አደር በአጠቃላይ ከህዝብ፣ ከመጽሐፍ፣ ከምሁራን...ይማራል። ከተግባርና ከማንኛውም ተሞክሮ ይማራል። ከሚያነባቸው፣ ከሚማራቸው ደግሞ ምርምር ጨምሮበት የህብረተሰብ ህይወት የሚለወጥበትን መንገድ ይተልማል።

ተመራምሮ የደረሰበትን ደግሞ ለሌሎች ያስተምራል። ሲያስተምር አይሰለችም፣ ከባድ ንድፈ ሃሳብን በቀላል መንገድ የማስረዳት ብቃት አለው።

**መለስና ልማት**

መለስ የአገራችን ልማት ፊት አውራሪ ነበር። አሁን ያሉት ልማቶች በህይወት በነበረበት ወቅት የሰጠው አመራር ውጤቶች ናቸው። ለአቅም ግንባታ ዩኒቨርሲቲዎች፣ የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ቤቶች...እንዲኖሩ ሠርቷል። ልማት ቁሳዊ ሀብት ማለት ብቻ አይደለም፣ ልማት ሰው ላይ የሚሠራ ሥራ ነው። ልማት ሲሠራ በሰውና በተፈጥሮ መካከል ተመጋጋቢ እንደሚሆን አድርጎ ነው።

«ድህነትን ለማስወገድ ተራራ መውጣት፤ ፋኖ ተሰማራ እያሉ መዘመር አያስፈልግም፤ ነገር ግን ይህን ለማድረግ ጥሩ ሞያተኛ፣ ጥሩ ግንበኛ፣ ጥሩ አናፂ...መሆን ይገባል። ዴሞክራሲያዊ አስተሳሰብ ያለው ወጣት መሆን ያስፈልጋል። ዕራስን ከተለያዩ ማህበራዊ ግድፈቶች ነፃ ማውጣትን ይጠይቃል።...የሚሠሩ እጆች፣ የሚያስብ ጭንቅላት፣ የወጣቱን ኃይል ይዘን ስንዴ የምንለምንበት ሁኔታ መቆም አለበት» ሲልም ወጣቱን በልማት ላይ እንዲሰማራ አነሣስቷል።

**ለሠላም የቆመ መሪ**

መለስ በ1981 ዓ.ም ያወጣው የሰላም ሃሳብ ሁሉንም የሚያሳትፍ የሽግግር መንግሥት መመስረትን ታሳቢ የሚያደርግ ነበር። ይህ ሃሳቡ ግን በሠራዊቱና በህዝብ ተቀባይነት አልነበረውም። መለስ ግን በወቅቱ ሁለት ሦስተኛ የአገሪቱ ክፍል በደርግ ስር ያለ መሆኑን፣ ጦርነት ሰውና ኢኮኖሚ የሚበላ መሆኑንና ደርግ በህይወት እያለ የሽግግር መንግሥት መመስረት ከተቻለ ደርግንም በፖለቲካ ትግል ለማሸነፍና ለማጋለጥ የሚጠቅም መሆኑን ከትግል ጓዶቹ ጋር ሆኖ አስተምሯል። ሰላም ለልማትና ዴሞክራሲ የግድ አስፈላጊ መሆኑን ሰብኳል። ይህ ሃሳብ በህዝብና በሠራዊቱ ተቀባይነት አግኝቶ የነበረ ቢሆንም በደርግ በኩል ተቀባትነት ባለማግኘቱ ደርግን በኃይል መደምሰስ ተችሏል።

ከደርግ ውድቀት በኋላም ቢሆን 25 የፖለቲካ ፓርቲዎች የተሳተፉበት 87 የምክር ቤት ወንበር ያለው የሽግግር መንግሥት ተመስርቷል። የኢህአዴግ ወንበር 32 የነበረ ቢሆንም አብላጫ ድምፅ ባልነበረበት ሁኔታ ነው መለስ እያሳመነ በሰላማዊ መንገድ መምራት የቻለው። የሽግግሩ ዘመን በሰላም እንዲጠናቀቅና ሕገ መንግሥት እንዲረቅም ብቁ አመራር ሰጥቷል።

ሠራዊት ህዝባዊና ለሰላም መቆም እንዳለበት፣ የውጭ ግንኙነቱም ማዕከሉ ሰላም መሆን ያለበት መሆኑን፣ በአካባቢያችን ሰላም ከሌለ ለኢትዮጵያም የማይበጅ መሆኑንም አስተምሯል።

**ሕገ መንግሥታዊነት**

ብሩሁ የመለስ አዕምሮ የኢትዮጵያ መፃኢ ዕድል በየትኛው የትግል መስመር ላይ ይመርኮዝ የሚለውን ሃሳብ ከማውጠንጠን አርፎም አያውቅም፡፡ አገር አቀፍና ዓለም አቀፍ ሁኔታዎችን ግምት ያስገቡ የትግል መስመሮች እንንደፍ በማለት፣ አማራጫችን በኢኮኖሚ መስክ መላው ህዝብ በየደረጃው ተጠቃሚ የሚሆንበት የነፃ ኢኮኖሚ ግንባታ መመስረት፣ በፖለቲካ መስክ የመድበለ ፓርቲ

መመስረት የሚሉት ሃሳቦችን፤ ሰላም፣ ዴሞክራሲና ልማት የማይነጣጠሉ የህልውናችን መሰረቶች ናቸው ብሎ አስተምሯል፡፡

ኢትዮጵያ ካልለማች በድህነት ትበታተናለች፤ በፍጥነት እናልማ፤ ያለ ሰላም ልማት አይኖርም፤ ሰላማችንን አስተማማኝ ለማድረግ ህዝቡን የልማት ተጠቃሚ እናድርገው፤ ያለዴሞክራሲ ልማት የለም፤ ዴሞክራሲው በሰፊ ህዝባዊ ተሳትፎ ላይ ይመስረት፤ ጥቂት ባለሥልጣኖች ብቻ ሳይሆኑ ከቀበሌ እስከ አገር አቀፍ በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ የህዝብ ተወካዮች ይኑሩን በማለት አጥብቆ አስተምሯል፡፡ የኢትዮጵያ ህዝቦች ለዘመናት የነበረውን መጥፎ ቅርስ ሽረው ተከባብረውና ፈቅደው አንድ የጋራ የኢኮኖሚና የፖለቲካ ማህበረሰብ ለመመስረት ያለሙበት፤ ዴሞክራሲያዊ ሕገ-መንግሥት ረቂቅ ሲዘጋጅ መለስ አንኳር የሆኑትን የሕገ መንግሥቱን መሰረተ ሃሳቦች በማስቀመጥ ረገድ ትልቅ አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡

**ማጠቃለያ**

ታላቁ መሪ መለስ ዜናዊ በ1971 ዓ.ም. በተካሄደው የህወሓት 1ኛ ድርጅታዊ ጉባኤ የማዕከላዊ ኮሚቴ አባል ሆኖ ተመረጠ፤ ይልቁኑ ደግሞ በ1975 ዓ.ም. በድጋሚ የእዚሁ ኮሚቴና የፖለቲካ ቢሮ አባል ሆኖ ከተመረጠ ወዲህ የትግራይን ህዝብና የኢትዮጵያን ህዝብ ትግል ትርጉም ባለው ሁኔታ ወደፊት ያራመዱ የፖለቲካ ተቋሞች እንዲነደፉ እጅግ የላቀ አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡

የመለስ ባለ ራዕይነት፣ የለውጥ አንቀሳቃሽነትና መሪነት ጐልቶ በየመድረኩ ለሚነሱት የፖለቲካ ጥያቄዎች በጥናት ላይ የተመረኮዙ ትንተናዎችና ወደ ተጨባጭ የተግባር መመሪያነትም ሊሸጋገሩ የሚችሉ አቅጣጫዎች በማስቀመጥ ብቃቱ ጐልተው ታይተዋል፡፡ ከእዚህም አኳያ በትግራይ ህዝብ ላይ የተጫኑት በደሎች በአስተማማኝ ሁኔታ ሊወገዱ የሚችሉት በኢትዮጵያ ህዝባዊ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ሲገነባ እንደሆነ፤ ለእዚህም በአገር አቀፍ ደረጃ የዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ህብረት ሊመሰረት እንደሚገባ አጥብቆ ሞግቷል፡፡

ህዝባዊ ወያነ ሓርነት ትግራይ (ህወሓት) በ1967 ተመስርቶ በትግል ላይ በቆየባቸው ቀጣይ 10 ዓመታት ውስጥ ምንም እንኳን እጅግ አስቸጋሪ ሁኔታዎችን አልፎ ህልውናውን ቢያረጋግጥም ትግሉን ወደፊት የማራመዱ ሁኔታ እጅግ አሳሳቢ ሆኖ ነበር፡፡ በዚህ ወቅት በኢትዮጵያ ህዝባዊ ዴሞክራሲያዊ አብዮት ግቦች፣ የትግል ስትራቴጂና ታክቲኮች እንዲሁም የኃይሎች አሰላለፍ፤ ትጥቅ ትግሉ በመሀል አገር የሚገኙ ህዝቦችን አንገብጋቢ ጥያቄዎች መሰረት አድርጐ አድማሱን ስለሚያሰፋባቸው አግባቦች ግልፅ አቅጣጫን አስቀምጧል፡፡

ከደርግ ውድቀት በኋላም የአገራችንን ብዙሕነት በአግባቡ የሚያስተናግድ፣ ሁሉንም ፖለቲካዊ ኃይሎች የሚያሳትፍና የኢትዮጵያ ብሔር፣ብሔረሰቦችና ህዝቦች ፈቅደው በመዋሃድ አዲሲቱን ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን እንዲገነቡ በብቃት የሚያዘጋጅ የሽግግር መንግሥት ካልመሰረትን ሥልጣን በያዝን ማግሥት ወደ ሌላ ጦርነት መግባታችን፣ አገራችንም የነዩጎዝላቪያ ዕጣ እንደሚገጥማት አይጠረጠርም በማለት ሞግቷል፡፡ ይህ ዕጣ እንዳይደርሳትም ሠርቷል። በሕገ መንግሥት የምትመራና ብዝሀነት ማስተናገድ የምትችል አገርም መገንባት ችሏል።

አገራችን ዛሬ ለደረሰችበት የዕድገትና የሽግግር መድረክ እንድትበቃና ጠንካራ መሰረት እንዲጣል ለማድረግ መለስ ግንባር ቀደሙን ሚና ተጫውቷል፡፡ ስለዚህ የባለ ምጡቅ አዕምሮው ታላቁ መሪ አስተምህሮዎች ትናንት ውጤታማ ነበሩ፣ ዛሬም እየተሠራባቸው ነው፣

ነገም ይሠራሉ።(ለዚህ ፅሁፍ የመለስ ዜናዊ አስተምህሮዎችና እሴቶች(ለውይይት የቀረበ)፣ ምስለ መለስ የማንነቱ ገፅታ  ሰነዶች